የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

# የስብሰባ ጥሪ

ጥቅምት 2007 ዓ. ም.

ዋና መቀመጫውን በጀርመን ሀገር በበርሊን ከተማ ያደረገው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢ.ፖ.እ.አ.ኮ)ን የምንደግፍ ከኢትዮጵያዊያንና ለኢትዮጵያ ወዳጅ ከሆኑ የጀርመን ዜጎችና እንዲሁም ለሰብአዊ መብት መከበር ከሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ተቋማት ጋር በ “ኢትዮጵያ ስለሚገኘው የሰብአዊ መብት ሁናቴ“ ለመወየየት አንድ ሕዝባዊ ስብሰባ በጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም. (ኖቬምበር 8 ቀን 2014 ዓ.ም.) በኑርንበርግ ከተማ አዘጋጅተናል።

እንደሚታወቀው የወያኔ ቡድን በምዕራቡ ኃያላን በተለይም በአሜሪካ መንግስት ሙሉ ድጋፍና ትብብር ከዛሬ 23 አመታት በፊት ከሥልጣን ከተቆናጠጠ ጀምሮ በዜጎቻችን ላይ እየደረሱ ያሉት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ከድጡ ወደ ማጡ በመሆናቸው ሕዝባችን ኑሮውን በአሳዛኝና አሰቃቂ ሁናቴ እንዲገፋ ተገዷል። ኢትዮጵያ ሀገራችን የጥቂቶች መንደላቀቂያ፤ ለብዙሃኑ ደግሞ ሲኦል መሆኗ በባሰ ሁናቴ ቀጣይ እንዲሆን ተደርጓል። ከተለጣፊዎችና ለአገዛዙ ቀና አመለካከት ካላቸው ጥቂት ቡድኖች በስተቀር በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ የሚያሰሙ ሀገር ወዳድ ኃይሎች ይጨቆናሉ፣ ይታፈናሉ፣ ለስደት ይዳረጋሉ፣ ደብዛቸው ከነጭራሱኑ የጠፋው የዜጎች ቁጥር በርካታ ነው። የእምነት ነፃነትም ሆነ እኩልነት አይከበርም። በተለያዩ የማፈኛ ማጎሪያዎች የሚሰቃዩት ዜጎቻችን ቁጥር ከ 45000 በላይ እንደሆነ የተለያዩ ለሰብአዊ መብት የሚንቀሳቀሱ ተቋማት የሚገልፁት ነው። በጎሳ ልዩነት ላይ የተመሰረተው የወያኔ አገዛዝ ፖሊሲ በተለይ በአማራው ብሔርሰብ አባላት ላይ የሚያደርሰው በደልና እመቃ አሳዛኝና አሰቃቂ ከመሆኑም በላይ እትብታቸው ከተቀበረበትና በሰላም ከሚኖሩበት አካባቢ በግዴታ እንዲፈናቀሉና ለከፍተኛ ስቃይ የተዳረጉት በርካታ ናቸው።

ዴሞክራሲ ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ካልሆነ በስተቀር ደብዛው ተፈልጎ የሚገኝ አይደለም። በነፃ መደራጀት ዘብጢያ ያስወርዳል። ነፃ ፕሬስ ባለመኖሩም ኃሳብን ያለምንም ፍራቻ በነፃ መግለፅ አደገኛ ለመሆኑ በቅርቡ ለእስር የተዳረጉት ጋዜጠኞችና ብሎገሮች የሚያመላክቱት ናቸው። የጸረ ሽብር ሕጉ በሀገር ወዳዱ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ሰላም ወዳድ ኃይሎች ጭምር ሽብርን የማይታደግና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን ለማፈኛ መሳሪያ ነው ተብሎ የተወገዘው የውጤቱ አስከፊነት በግልፅ እየታየ ነው። በሚደርሰው በደልና ጭቆና የተነሳ ሀገር ተረካቢና የእድገት ኃይል ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ በርካታ ወጣት ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ አቅጣጫዎች ለስደት በመዳረጋቸው በጉዞአቸው ሂደት ያጋጠሟቸው የሰውነት አካላቸውን ከመነጠቅ አንስቶ የደረሱባቸው ጉስቁልናዎች፤ የአስገድዶ መድፈር ተግባራት፤ ጥሪታቸውን መዘረፈና መደብደብ ሕይወታቸው ሊተርፍ ከቻሉት ውስጭ በርካታዎቹን ለሕሊና ቀውስ ዳርጓቸዋል። ሰቀቀን ለቆባቸዋል። በድንበር አሻጋሪ ሕገወጥ ቀማኞችና ወረበሎች ለባሕር ማዕበል ፍፁም ተጋላጭ በሆኑ ታንኳዎችና ጀልባዎች ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ በመጫን ለማቋረጥ በሚያደርጉት ጥረት ከባሕር ሰምጠው ሕይወታቸው የጠፋው በርካታ ናቸው።


SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG, MB R2P 227, CANADA
E MAIL: SOCEPP@AOL.COM / info@socepp.info
WEB SITE: WWW.SOCEPP.INFO

- 1 -

በመሆኑም እኛ የኢ.ፖ.እ.አ.ኮ ደጋፊ ኢትዮጵያዊያን እነኝህን በሰብአዊ መብት ጥሰት ምክንያት እየደረሱ ያሉ ሁናቴዎችን ለመወያየትና ለችግሩም በጋራ መፍትሄ ለማፈላለግ፤ በሚደረጉት እንቅስቃሴዎችም የራሳችንን አስተዋፅዖ ለማበርከት ይቻለን ዘንድ ይህንን የውይይት ስብሰባ አዘጋጅተናል። በውይይቱ ውጤት ላይ በመመርኮዝም ሕዝባችን ለነፃነቱ መጎናፀፍ፤ ለፍትህ መረጋገጥ፤ ለሰላም መስፈን፤ ለመብት መከበር የሚያደርጋቸውን እንቅስቃሴዎቹን በሁለመና መልኩ ለመደገፍ ይቻለን ዘንድ የተዘጋጀው ይህ ስብሰባ የምንመካከርበት ይሆናል።

በዚህ የውይይት ስብሰባ የመንደርደሪያ ሃሳብ የሚያቀርቡልን፤

1. ለረጅም ጊዜያት ያለማቋረጥ እስካሁን ድረስ ለሰብአዊ መብት መከበር ተከራካሪ የሆኑት፤ በሚደርሱት ግጥማቸው በበርካታ ኢትዮጵያን ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፉትና የኮሚቴው ሊቀ መንበር የሆኑት አቶ አሊ ሁሴን፤

2. በካናዳ በዊኒፔግ ከተማ የሁለት የክብር ሽልማት ባለቤት የሆኑትና የአባታቸውን ፈለግ በመከተል ለመብት መከበር የሚንቀሳቀሱት ልጃቸው ወጣት ምሳሌ አሊ በክብር እንግድነት በስብሰባችን ላይ ይገኛሉ።

| | |
|---|---|
| የስብሰባው ቀን | ቅዳሜ ኖቬምበር 8 ቀን 2014 ዓ.ም. |
| ቦታው | **Stadt Nürenberg Nachbaschfthaus Gostenhof** |
| | **Adam-Klein-Str.6** |
| | **90429 Nürenberg** |
| ሰአት | **ከቀኑ 12.00 ሰአት ጀምሮ ይሆናል።** |

በመሆኑም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ስብሰባ በመገኘት የውይይቱ ተካፋይ በመሆን የራሳችሁን ቀና አስተዋፅጽዖ ታበረክቱ ዘንድ የከበረ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የኢ.ፖ.እ.አ.ኮ. ደጋፊዎች